Oct 8, 2013

# የቃሉ ሀይል

የእግዚአብሄር ቃል ሀይል አለው፡፡ኢሳ 55፡10-11 ላይ <<ከእኔ አፍ የሚወጣው ቃል፤ መንፈስ የሆነው ቃል ወይም የጊዜው ቃል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትን ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም>> ይላል፡፡እውነት ነው መንፈስ የሆነው ቃል ከአፉ ከወጣ ብዙ ስራን ይሰራል፡፡አብዛኞቻችን ወደ እርሱ የመጣነው በአንድ አጋጣሚ ይህ የተሳለ ቃል ወስጣችን መተከያና መብቀያ ቦታ ስላገኘ ነው፡፡የእግዚአብሄር ቃል እብ 4፡12-16 ላይ ሲገልጸው የሚሰራ እና ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ የተሳለ እና ወደ ጠለቀው ማንነታችን ዘልቆ ልባችንን እንደሚመረምር እና በእርሱ ፊት ሁሉ ነገር የተገለጠ እና የተራቆተ እንደሆነ ይናገራል፡፡አዎ የሚሰራ ነው፡፡ቃሉ ነፍስን ይመልሳል፣ደስታን ይሰጣል፣ከጥፋት ያወጣል ወዘተ፡፡

ምሳ 15፡23-24 <<ቃልም በጊዜው ምንኛ መልካም ነው፡፡በታች ካለው ከሲኦል ያመልጥ ዘንድ የህይወት መንገድ አስተዋዩን ሰው ወደ ላይ ይወስደዋል>>ይላል፡፡<<ቃልም በጊዜው ምንኛ መልካም ነው>>የሚለው ሀሳብ በጊዜው ወይንም በሚፈለግበት ሰአት በእግዚአብሄር መንፈስ ስለተነገረ ሬማ ስለሆነው የእግዚአብሄር ቃል ነው የሚናገረው፡፡የእንደዚህን አይነት ቃል ወደነት ሲናገር <<ምንኛ መልካም ነው>>ይለዋል፡፡ማለትም ስራን የሚሰራ፣ለውጥን የሚያመጣ፣ካለንበት ማጥ የሚያወጣ ባለወለታ የሆነ ቃል እንደሆነ ነው የሚያሳየን፡፡ይህ ቃል ከሚቀጥለው ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ያለው ይመስላል፡፡ይህ ቃል ነው ከሲኦል የሚያስመልጠው፡፡<<ወደ ላይ ይወስደዋል>>የሚለው ሀሳብ መንፈስ የሆነው ቃል ብርቱ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ምሳ 13፡14 ላይ ከዚህ ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡እንዲህ ይላል፡-<<ሰው ከሞት ወጥመድ ያመልጥ ዘንድ የጠቢብ ሰው ትምህርት የህይወት ምንጭ ነው፡፡>>ቃሉ የማየትን ጸጋ በመስጠትና አቅጣጫ በመለወጥ ከብዙ ወደ ሞት ከሚወስዱ ወጥመዶች ያስመልጠናል፡፡

ዮሀ 8፡31-32 እንዲህ ይላል፡-<<እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል፡፡>>አዎ የቃሉን ሀይል በህይወቴ አይቼዋለሁ፡፡ለቃሉ የሚገባውን ጊዜና ልብ ከሰጠን ከብዙ ጉድ ያወጣናል፡፡በተግባር ደረጃ ይህ የህይወት ቃል ወደ ወስጤ በመግባቱ ከሀጢያት፣ከመጠጥ፣ከጫት እና ከሲጋራ ሱስ መንጭቆ አወጥቶኛል፡፡እላዬ ላይ የነበረው የሱስ ቀንበር ቀላል አልነበረም ግን ይህ ሀይል ያለው ቃል ማሉ በሙሉ ነጻ አድርጎኝ በነጻነት ተለቅቄ ያለ ምንም ባርነት እየኖርኩ እገኛለሁ፡፡

የጠላትንም ተግዳሮት የምናሸንፍበት ዋና መሳሪያችን ይህ ሀይል ያለው የእግዚአብሄር ቃል ነው፡፡መዝ 45፡5 ላይ እንዲህ ይላል፡-<<ሀያል ሆይ ፍላጻዎችህ የተሳሉ ናቸው እነርሱም በንጉስ ጠላቶች ልብ ወስጥ ይገባሉ አህዛብም በበታችህ ይወድቃሉ>>ይህ ቃል የሚናገረው ሬማ ሆኖ በአፋችን ላይ ስለተዘጋጀው ቃል ነው የሚናገረው፡፡በሕይወታችን ሬማ የሆነ ቃል ደግሞ ማንኛውንም ተግዳሮት ጥሶ የመግባትና ነገሮችን የመለወጥ ችሎታ አለው፡፡የአጋንንትን ሚብና እቅድም መቆራረጥ ይችላል፡፡አንድ ወቅት የምሰራበት ቦታ የሚደመቅ ነበረና ወደ ጌታ በዛ ጉዳይ እጸልይ ነበር፡፡አንድ ፓስተር ወደ ምሰራበት በሮ መጥቶ ልጸልይልህ አለኝና <<የጌታ መንፈስ ጠላቶችን አጠፉሁልህ ይልሀል>>ብሎ የሚደንቅ መንፈሳዊ መልእክት ነግሮኝ ሄደ፡፡ያ መልእክት የጊዜው መልእክት ስለነበር ልረሳው በማልችለው ሁኔታ አሁንም ልቤ ወስጥ ተቀርቅሮ አለ፡፡ከዚያ በኋላ በትንሽ ጊዜ ወስጥ ያን ቦታ ለቅቄ በብዙ መስፈርት የሚሻል ቦታ መስራት ጀመርሁ፡፡የጊዜው ቃል ሲመጣ ነገሮችን በፍጥነት የመለወጥ ችሎታ አለው፡፡

ቃሉ ለህይወታችን ወብትን የመስጠት ችሎታ አለው፡፡መዝ 119፡73 ላይ<<እጆችህ ሰሩኝ አበጃጁኝም>> እንደሚል ቃሉ እያቀና እና እያስተካከለ ፍጻሜችን ይለውጣል፡፡በጥበብ በሞገስ በእምነት እና በፍቅር እንድናድግ እያደረገ ደምቆ የሚታይ መልእክት ያደርገናል፡፡እጅግ የምወደው ይህንን ሀሳብ የሚገልጽ ሀሳብ መዝ 51፡18 ላይ ይገኛል፡-<<አቤቱ በወደታህ ጽዮንን አሰማምራት የኢያሩሳሌምን ቅጽሮች ስራ፡፡የጽድቁን መስዋእት መባውንም የሚቃጠለውንም መስዋእት በወደድህ ጊዜ ያን ጊዜ በመሰዊያህ ላይ ፍሪዳዎችን ይሰዋሉ፡፡>>የእግዚአብሄር ቃል ወስጣችን በመስራትና በመቀየር እንደ እርሱ ፈቃድ የሆነ መስዋእትን እና አምልኮ እንድንሰዋ ያደርገናል፡፡ወስጣችን በሚገባ ሳይሰራ የምንሰዋው መስዋእት ምስጋናም ሆነ አምልኮ ከጣራ አያልፍም፡፡ነገር ግን ለቃሉ ያልተከፋፈለ ልብን ሰጥተን በበቂ ሁኔታ ከከተማብነው ካጠፍነው እና ካሰላሰልነው ወስጣችንን ከምናስበው በላይ ያሰማምረዋል፡፡ስለዚህም አምልኮአችን እና ስግደታችን እውነተኛ(authentic) እና በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ይሆናል፡፡ጌታ ሆይ ፍጻሜዎቻችንን የሚያሳምረውን የቃልህን ደጆች ከፈትልን፤በቃልህ ወስጥ ያለውን እንቁ እንድናይ አብራልን!